# ትምህርት 7

1. እግዚአብሔር ከመፍጠሩ በፊት ዓለም ምን ይመስል ነበር?

ሀ- በመጀመሪያ ብርሃን አልነበረም።

ለ- በመጀመሪያ ጨለማ ምድርን ሁሉ ሸፍኖት ነበር።

2. እግዚአብሔር ብርሃንን በአንደኛው ቀን የፈጠረው እንዴት ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ብርሃንን የፈጠረው በመናገር ብቻ።

3. እግዚአብሔር በሁለተኛው ቀን ጠፈርን (ሰማይን) የፈጠረው እንዴት ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ጠፈርን (ሰማይን) የፈጠረው በመናገር ብቻ ነበር።

4. እግዚአብሔር መሬትን የሸፈነውን ውኃ የለየው እንዴት ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ከፊሉን ውኃ ከጠፈር በላይ አኖረው።

ለ- እግዚአብሔር ቀሪውን ውኃ በምድር ላይ ተወው።

5. ደረቅ ምድር ይታይ ዘንድ ውኃው ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ያዘዘው ማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ነው።

6. እግዚአብሔር ውኃው ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ ማዘዝ የቻለውና ወኃውም የታዘዘው በምን ምክንያት ነው?

ሀ- ምክንያቱም ውሃን የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

7. እግዚአብሔር ተክሎችንና ዛፎችን የፈጠረው እንዴት ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ተክሎችንና ዛፎችን ሁሉ የፈጠረው በመናገር ብቻ ነው።

8. እግዚአብሔር ተክሎችንና ዛፎችን ሁሉ የፈጠረው ለማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር የፈጠራቸው ለእኛ ለሰዎች ነው።

9. እግዚአብሔር ተክሎችንና ዛፎችን ለምን ፈጠራቸው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን እጅግ ስለሚወደን ነው።

10. እግዚአብሔር ፀሐይን ጨረቃንና ከዋክብትን የፈጠራቸው እንዴት ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ፀሐይን ጨረቃን እና ከዋክብትን የፈጠረው በመናገር ብቻ ነው።

11. እግዚአብሔር ዓሦችንና ወፎችን ሁሉ የፈጠረው እንዴት ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ዓሦችንና ወፎችን ሁሉ የፈጠረው በመናገር ብቻ ነበር።

12. እግዚአብሔር ዓሦችንና ወፎችን ሁሉ የፈጠረው ለማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር የፈጠራቸው ለእኛ ለሰዎች ነው።

13. እግዚአብሔር ሁሉንም ዓሦችና ወፎች የፈጠረው ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን እጅግ ስለሚወደን ነው።

14. እግዚአብሔር ስለ ፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ ምን አለ?

ሀ- እግዚአብሔር ሁሉም ነገር «መልካም ነው» አለ።

15. እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች ፍጹም አድርጎ ሊፈጥራቸው የቻለው እንዴት ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር በስድስተኛው ቀን ምንን ፈጠረ?

ዘፍጥረት 1፡24-25

24- እግዚአብሔር፥ «ምድር ሕያዋን ፍጡራንን እንደየወገናቸው ከብቶችን፣ በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንን፣ የዱር እንስሳትን፣ እያንዳንዱን እንደ ወገኑ ታስገኝ» አለ፤ እንዳለውም ሆነ።

25- እግዚአብሔር የዱር እንስሳትን እንደየወገናቸው፣ ከብቶችን እንደየወገናቸው፣ እንዲሁም በምድር ላይ የሚሳቡ ፍጡራንን እንደየወገናቸው አደረገ። እግዚአብሔርም ይህ መልካም እንደ ሆነ አየ።

- በስድስተኛው ቀን እግዚአብሔር እንስሳትን ሁሉ ፈጠረ።

- እግዚአብሔር ስንት ዓይነት እንስሳትን ፈጠረ?

- እጅግ ብዙ ናቸው።

- እንስሳትን ሁሉ መፍጠር የሚችለው ማን ነው?

- እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እንስሳትን መፍጠር የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር እንስሳትን መፍጠሩን ባጠናቀቀ ጊዜ ምድር ተዘጋጅታ ነበር።

- እግዚአብሔር ምድርን ያዘጋጀው ለመላእክት ወይም ለሰይጣንና ለአጋንንቱ ነው?

- አይደለም።

- ታዲያ እግዚአብሔር ምድርን ያዘጋጀው ለማን ነው?

- እግዚአብሔር ምድርን ያዘጋጀው ለእኛ ለሰዎች ነው።

- እግዚአብሔር እኛ ሰዎችን እጅግ ስለሚወደን፣ ፍጹም የሆነውን ምድር አዘጋጅቶልናል።

- እግዚአብሔር ምድርን ለመላእክት አላዘጋጀም።
- እግዚአብሔር ምድርን ለአጋንንት አላዘጋጀም።
- እግዚአብሔር ምድርን ለሰይጣን አላዘጋጀም።

- እግዚአብሔር ምድርን ያዘጋጀው ለእኛ ለሰዎች ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር ምድርን ለእኛ ለሰዎች ካዘጋጀ በኋላ የተናገረውን እናንብብ።

ዘፍጥረት 1፡26

26- እግዚአብሔር «ሰውን በመልካችን በአምሳላችን እንሥራ። በባሕር ዓሦች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር ሁሉ ላይ እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው» አለ።

- እግዚአብሔር «ሰውን በአምሳላችን እንፍጠር» አለ።

- እግዚአብሔር ለማን ነበር ይህን የተናገረው?

- እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።

- እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እርስ በርሳቸው እኛ ሰዎችን በአምሳላቸው ስለ መፍጠር ይነጋገሩ ነበር።

- እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ምንድን ነው?

- ሰው ነው።

- እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረት ሁሉ ሰዎች እጅግ አስፈላጊዎች በመሆናቸው፥ እግዚአብሔር ሰውን እንዴት አድርጎ ለመፍጠር ወሰነ?

- እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ለመፍጠር ወሰነ።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ከእንስሳት የተለዩ አድርጎ የፈጠራቸው እንዴት ነበር?

- እግዚአብሔር ሰዎችን በአምሳሉ ፈጠረ እንስሳት ግን የእግዚአብሔር አምሳል የላቸውም።

- «ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠሩ» ማለት ምን ማለት ነው?

- በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ይህ የሚታየው አካላችን አይደለም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሥጋና አጥንት ያለበት አካል የለውም።

- በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው አካላችን የማይታየው አካል ነው።

- በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው ነፍሳችን ነው።

- ነፍሳችን ሦስት ክፍሎች አሉት።

- ነፍሳችን አእምሮ ስሜትና ፈቃድ አለው።

- አእምሮአችን፥ ስሜታችንና ፈቃዳችን በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው።

- ከሰዎች አካል የትኛው ክፍል ነው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው?

- አእምሮአችን፣ ስሜታችንና ፈቃዳችን ነው።

- እግዚአብሔር በራሱ አምሳል ከፈጠረው የአካል ክፍል አንዱ አእምሮአችን ነው።

- እግዚአብሔር አእምሮ ስላለው፣ ሰውንም የፈጠረው አእምሮ ያለው አድርጎ ነው።

- እግዚአብሔር ማሰብ ስለሚችል፥ እኛም እንድናስብ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር በአእምሮአችን ምን እንድናደርግ ይፈልጋል?

- እግዚአብሔር በአእምሮአችን መልካሙን ሁሉ እንድናስብ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር ስለ እርሱ እንድናስብ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር ስለ እርሱ እንድናስብና እርሱን እንድናውቅ ይፈልጋል።

- ሰዎች በማይኖሩበት ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ ከእንስሳት ጋር ለመኖር ትፈልጋላችሁ?

- አዎን አትፈልጉም።
- ለምን?

- ምክንያቱም እንስሳት ማሰብም ሆነ መናገር ስለማይችሉ ነው።

- ከጓደኞቻችን ጋር እንደምንነጋገረው ሁሉ፣ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር እንድንነጋገር ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር አእምሮ አለው፣ ሰዎችንም ሲፈጥር አእምሮ ሰጥቷቸው ነው።

- እግዚአብሔር እርሱን ማወቅ እንድንችል አእምሮ ሰጥቶናል።

- እግዚአብሔር በእርሱ አምሳል የፈጠረው ሁለተኛው ክፍል ስሜታችን ነው።

- እግዚአብሔር ስሜት ስላለው፣ እኛንም ስሜት ያለን አድርጎ ፈጠረን።

- እግዚአብሔር መደሰት ይችላል፣ እኛም ደስ እንድንሰኝ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር በእርሱ ደስ እንድንሰኝ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር እርሱን እንድንወደው ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር መጥላትንም ይችላል።

- እግዚአብሔር ምንን ይጠላል?

- እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ይጠላል።

- ኃጢአት ምንድን ነው?

- ኃጢአት እግዚአብሔር የማይፈልገው ነገር ነው።
- ኃጢአት እግዚአብሔር የማይፈልገው ነገር ሁሉ ነው።

- እግዚአብሔር ማዘን ይችላል።

- እግዚአብሔር በምን ያዝናል?

- እግዚአብሔር እርሱን በማይወዱት ሰዎች ያዝናል።

- እናንተ ልጆቻችሁን እንደምትወዱ፣ እንዲሁ እግዚአብሔር ይወዳችኋል።

- እግዚአብሔር ስሜት ስላለው፣ እኛንም ስሜት ያለን አድርጎ ፈጠረን።

- እግዚአብሔር ስሜት የሰጠን ለምንድን ነው?

- እርሱን እንድንወደው ነው።

- እግዚአብሔር በራሱ አምሳል የፈጠረው ሦስተኛው ክፍል ፈቃዳችን ነው።

- እግዚአብሔር ፈቃድ ስላለው፣ እኛንም ፈቃድ እንዲኖረን አድርጎ ፈጠረን።

- እግዚአብሔር መምረጥ ይችላል እኛም ምርጫ እንድናደርግ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር በፈቃዳችን ምን እንድናደርግበት ይፈልጋል?

- እግዚአብሔር በፈቃዳችን መልካሙን እንድንመርጥ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር እርሱን እንድንመርጥ ይፈልጋል።

- እግዚአብሔር እርሱን እንድንመርጠውና ለሕይወታችን መልካም እንዲሆን ይፈልጋል።

- ጠመንጃ በምትተኩስበት ጊዜ ምን መምታት እንዳለብህ ጠመንጃው ይመርጣል?

- አዎን አይመርጥም።
- ለምን አይመርጥም?

- ምክንያቱም ጠመንጃ ፈቃድ ስለሌለው ነው።

- ጀልባችሁን በውኃ ላይ በምትቀዝፉበት ጊዜ፣ ጀልባው ወዴት መሄድ እንዳለባችሁ ይመርጣል?

- አዎን አይመርጥም።
- ለምን?

- ምክንያቱም ጀልባ ፈቃድ ስለሌለው ነው።

- እግዚአብሔር ፈቃድ አለው፣ እኛንም ፈቃድ እንዲኖረን አድርጎ ፈጠሮናል።

- እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲኖረን እድርጎ ስለፈጠረን እርሱን መምረጥ እንችላለን።

- እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው ስለ መፍጠሩ (እስቲ) እናንብብ፡

ዘፍጥረት 1፡27

27- ስለዚህ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው። በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።

- እግዚአብሔር በመጀመሪያ ስንት ሰዎችን ፈጠረ?

- አንድ ወንድና አንዷት ሴት ብቻ ፈጠረ።

- በቅድሚያ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው ፈጠረ።

- ከዚያም እግዚአብሔር የመጀመሪያዋን ሴት ፈጠረ።

- የመጀመሪያው ሰው ስም ማን ነበር?
- አዳም።

- የመጀመሪያውን ሰውና ሴት ማፍጠር የቻለው ማን ነው?

- እግዚአብሔር ነው።

- ሰውን መፍጠር የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ዘፍጥረት 2፡7ሀ

7- እግዚአብሔር አምላክም ከምድር አፈር ወስዶ ሰውን አበጀው።

- እግዚአብሔር አዳምን ከምድር ዐፈር ፈጠረው።
- አዳም ወዲያው ሕያው ያልሆነው ለምንድነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር እስትንፋሱን በአዳም ውስጥ ገና እፍ ስላላለበት ነበር።

ዘፍጥረት 2፥7ለ

7- እግዚአብሔር አምላክ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ።

- አዳም ሕያው የሆነው እግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስ እፍ ካለበት በኋላ ነበር።

- በሰዎች ውስጥ ሕይወትን እፍ ማለት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- ሕይወት መስጠት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- አዳም የሰው ዘር ሁሉ የመጀመሪያ ነው።
- አዳም የሰው ዘር ሁሉ አባት ነው።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰዎችን ነጭና ጥቁር አድርጎ አልፈጠረም።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር የፈጠረው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ብቻ ነው።

- ሁሉም ሰው የመጣው ከአዳም ነው።

- ሁሉም ሰው የአዳም ዘር ነው።

- እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረው በኋላ ምን ስልጣን ሰጠው?

ዘፍጥረት 1፡28

28- እግዚአብሔርም፣ «ብዙ ተባዙ፣ ምድርንም ሙሉአት፣ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች፣ እንዲሁም በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሕያዋን ፍጥረት ሁሉ ግዙአቸው» ብሎ ባረካቸው።

- እግዚአብሔር አዳምን በምድር ሁሉ ላይ አለቃ አደረገው።

- መላእክት ለምን በምድር ላይ አለቃ አልሆኑም?